## ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ግንቦት 9 ቀን 2001 ዓ. ም.)

**የታሰሩት ከፍተኛ መኮንኖች ፍርድ ቤት ቀርበው በ10 ደቂቃ ጊዜ ቀጠሮ ተሰጥቶዋቸው ተመለሱ፣ ይፈለጋሉ የተባሉት ሰዎች በወያኔ እስር ቤት የነበሩ መሆናቸው ታወቀ፣ ሚሳኤሎችን ጨምሮ በርካታ ከባድ የጦር መሳሪያዎች ወደ ጎንደር ተጉዋጉዋዙ፣ የወያኔ ካድሬዎች በተለያዩ የጦር ካምፕ ውስጥ ግምገማ ጀመሩ >>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>**

**ከፍኖተ-ኅብረት የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ሌላም ዜናና ሐተታ ያንብቡ ……………….**

**የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ አድርገዋል፣ ለጥቆ ደግሞ የወያኔን ባለስልጣናት ለመግደል አሲረዋል ተብሎ የታሰሩት 40 ሰዎች ሰኞ ግንቦት 3 ቀን 2001 ዓ.ም. ከሰዓት በሁዋላ በአራዳ ምድብ ችሎት ቀርበው መመለሳቸው ታወቀ::**

**ሰኞ ዕለት የታሳሪ ቤተሰቦች በፍርድ ቤት ግቢ ውስጥ ከጠዋቱ 2 ሰዓት ጀምሮ ሲጠባባቁ የቆዩ ቢሆንም እስረኞቹን 8 ሰዓት ተኩል ሲሆን የማዕከላዊ ምርመራ ፖሊሶች ይዘዋቸው መምጣታቸውም ታውቆዋል::**

**ችሎት ከቀረቡ በሁዋላ እስረኞቹን ይዞ የቀረበው መርማሪ ምርመራዬን ስላልጨረስኩ እና ተጠርጣሪ ግለሰቦች ስላሉ እነሱን እስክይዝ ድረስ የ14 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ይሰጠኝ በማለት ጥያቄ በማቅረቡ ዳኛ ውም የ11 ቀን ቀጠሮ ሰጥቶት ለግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ. ም. መቅጠሩ ታውቆዋል::**

**በዕለቱ ከማዕከላዊ ምርመራ በሽፍን መኪና ታጉረው የመጡት እነዚሁ ታሳሪዎች ችሎት ለተሰየመው ዳኛ ጥያቄ ለማቅረብና እውነታውን ይፋ ለማድረግ ብሎም የወያኔን ድራማ ሊያፍረጠርጡ እጃቸውን ቢያወጡም አድማጭ እና ተመልካች በማጣታቸው ሀሳባቸውን ሳያቀርቡ ተከልክለው የተመለሱ ሲሆን በበረከት ስምኦን የሚመራው የወያኔ የኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤት በበኩሉ በዛው እለት ተፈላጊ ናቸው በሚል 3 ሰዎችን በምስል አስደግፎ በቴሌቪዥን ማሳየቱ ታውቆዋል::**

**ይፈለጋሉ ብለው እነ በረከት በቴሌቪዥን ይፋ  ካወጡዋቸው መካከል አንዱ ኮሎኔል አለበል አማረ የተባለው የአግአዚ ክፍለ ጦር የአስተዳደር መምሪያ ኃላፊ የነበረ ነው።  ይህ መኮንን በ1998 ዓ.ም. ከስራ ገበታው ላይ እያለ ትፈለጋለህ ተብሎ ቤተ መንግስት ምድር ቤት እስር ቤት ውስጥ የታሰረ መሆኑና እስከአሁን የት እንደደረሰ ቤተሰቦቹ ጭምር ባላወቁበት ሁኔታ መልሰው እራሳቸው ይፈለጋል ብለው በይፋ መግለጫ መስጠታቸው የወያኔ ድብቅ ተልእኮ የተጋለጠበት ነው ሲል ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::**

ይፈለጋሉ ተብሎ ስም ዝርዝራቸውና ምስላቸው የተገለፁት ሶስት ሰዎች ኮሎኔል አለበል አማረ፣ መሀመድ አባሜጫ እና አወቀ አፈወርቅ እንደሆኑ ተገልፆዋል:: መሀመድ አባሜጫ የተባለውም ተፈላጊ ግለሰብ ከሶስት ዓመት በፊት የኦነግ አባል ነህ ተብሎ ድብቅ እስር ቤት ታስሮ የነበረና እስከአሁን የት እንዳለ የማይታወቅ ሲሆን ዛሬ ግን ይፈለጋል ተብሎ ምስሉ ይፋ የተደረገ መሆኑ ሌላው አሳዛኙ ትርዒት መሆኑን ዘገባው አስታውሶዋል:: የወያኔ ባለስልጣናት ከዚህ ቀደም አስረው የገደሉዋቸውን ሰዎች ዛሬ እንደጠፉ አስመስለው ይፈለጋሉ እያሉ መግለጫ ማውጣታቸው እራሳቸውን ከማጋለጣቸውም በላይ ህዝብን ለማታለል እየተጠቀሙበት ያለው ስልት መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል:::

በአሁኑ ሰዓት በአንድ ብሔር ላይ ያነጣጠረው የእስራት እና የማዋከብ ዘመቻ ቀጥሉዋል። በተለይ በንግድ ስራ ላይ ብዙ ዓመታት ያሳለፉ የአማራ ተወላጆች ሰበብ እየተፈለገላቸው ወደ ዘብጥያ እያወረዱዋቸው መሆኑ ታውቆዋል:: በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የአማራ ብሔር ተወላጅ በሆኑት ላይ እጅግ መጠነ ሰፊ የሆነ የእስራት ዘመቻ እየተደረገ ከመሆኑም በላይ በነጋዴዎቹ ላይ የሙስና ወንጀል እየተባለ እንደሚታሰሩም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

ከዚህ ቀደም በመንግስት ባንኮች ውስጥ ሲሰሩ ቆይተው በአሁኑ ሰዓት የራሳቸውን የንግድ ተቋዋማት ከፍተው ሀብታም የሆኑ የአማራ ብሄር ተወላጆች በሙስና ምክንያት ለእስር ተዳርገው በፍርድ ቤት ዋስትና ከእስር ቢለቀቁም በደህንነቱ ባለስልጣን በጌታቸው አሰፋና በማዕከላዊ ምርመራ ዋና አዛዥ ታደሰ መሰረት ትዕዛዝ ከቃሊቲ እስር ቤት ሲወጡ በሩ ላይ ታፍነው በድጋሚ ወደ መአዕከላዊ እስር ቤት መግባታቸውን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በተመሳሳይ በባህር ዳር፣ በደሴ፣ በደብረ ብርሀን እና በሌሎችም የአማራ ክልል ከተሞች ያሉትን ነጋዴዎች ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ወግናችሁ እርዳታና ድጋፍ እያደረጋችሁ መሆኑ ስለተደረሰበት የንግድ ፍቃዳችሁ እስኪሰረዝ ድረስ የተተመነባችሁን ግብር በአስቸኩዋይ ክፈሉ እየተባሉ እየተዋከቡ መሆኑን ከባህር ዳር የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

የአምናውን ግብር ለመክፈል መስከረም ወር ላይ ወደ ንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሄደው የነበሩት የአማራ ክልል ነጋዴዎች ብዙዎቹ የተተመነባቸው ግብር ከአቅማቸው ጋር ተመጠጣጣኝ ያልሆነና ያልሰሩበትን ገንዘብ እንዲከፍሉ ከመደረጉም ሌላ የሚሰሩበት የንግድ ስራ በአግባቡ ሳይገለፅ በደፈናው ግብር ክፈሉ ተብለው የነበረ ሲሆን ይህም እንዲስተካከል ጥያቄ አቅርበው በእንጥልጥል ላይ የነበረ ቢሆንም በቅርቡ ግን የተወሰነባችሁን መክፈል ግዴታችሁ ነው አለበለዚያ ግን በግዴታ የንግድ ቦታዎቻችሁን ትለቃላችሁ እየተባሉ በግዴታ እንዲከፍሉ እየተደረጉ መሆኑንም የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

ለብዙ አመታት በዳኝነት ሲሰራ የነበረውና አሁን በጥብቅና ስራ ላይ የሚገኘው ጎሹ ይራድ የተባለውን የደጀን አካባቢ ተወላጅ ከወቅቱ ፖለቲካ ጋር አያይዘው ለእስር የዳረጉት ሲሆን በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሎጀስቲክ ክፍል ኃላፊ አቶ ጎሹ ደበበ የተባለውን የባንክ ባለሙያንም ላልተወሰነ ጊዜ ከስራ ውጭ እንዲሆን እና በቁም እስር ላይ እንዲቆይ ማድረጋቸው ታውቆዋል::

የወያኔ ቡድን ሰሞኑን ቁጥሩ የበዛ የከባድ መሳሪያዎችን እና ሚሳኤሎችን አስጭኖ ወደ ጎንደር እያጉዋጉዋዘ መሆኑ ታውቆዋል:: በሁለት ተከታታይ ቀናት ከ40 በላይ ታንክ እና ከ15 በላይ ሚሳኤል መግባቱንም የአይን እማኞቹን ዋቢ አድርጎ ምንጫችን ገልፆዋል::

ደርግ ከህዝብ ጉሮሮ ላይ እየነጠቀ ከወዳጁ ራሺያ ላይ በውድ ዋጋ ሚሳኤሎችንና ከባድ መሳሪያዎቹን እየገዛ መልሶ ህዝብን ሲረግጥ የነበረ ሲሆን አሁንም ወያኔ ከደርግ በባሰ መልኩ ከህዝቡ አፍ ላይ ነጥቆ እጅግ ዘመናዊ የተባሉ የጦር መሳሪያዎችን ከጊዜያዊ ወዳጁ ቻይና እና ከዩክሬን ላይ ሚሳዔሎችን ጭምር እየገዛ ህዝቡን ጨፍልቆ ለመግዛት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑም ታውቆዋል::

በጥብቅ ጥበቃ እና አጀብ የተጉዋጉዋዘው ይሄው ከባድ መሳሪያ ከአዲስ አበባ አርብ ሚያዚያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም. ሌሊት ተነስቶ ማክሰኞ እለት ግንቦት 4 ቀን 2001 ዓ.ም. ጎንደር የደረሰ መሆኑን የገለፁት የአይን እማኞቹ በተለይ አጃቢ ወታደሮቹ የከባድ መሳሪያውን ህዝብ እንዳያየው ጫካ ውስጥ እየደበቁ እንደነበርም ጨምረው ገልፀዋል::

የወያኔ ቡድን በጎንደር በኩል ከፍተኛ ስጋት ስላደረበት ከአባይ ድልድይ በሁዋላ ብዙ መቆጣጠሪያ ኬላዎችን ሰርቶ ተጉዋዦቹን ጥብቅ ፍተሻ እያደረገባቸው መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

ብዙ ቦታ በፍርሀት ባቁዋቁዋመው ኬላ አማካኝነት እየፈተሸ ያለው የወያኔ ቡድን ወደ ጎንደር የሚገባና የሚወጣ እድሜው ከ35 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ወጣት ለጥያቄ ትፈለጋለህ እየተባለ ለሰዓታት እየታሰረ እንደሚለቀቅም ዘገባው አብራርቶዋል::

የሽሬ ከተማ የሰዓት እላፊ የተጣለበት ሲሆን ማንኛውም የከተማዋ ነዋሪ ከምሽቱ አንድ ሰዓተት በሁዋላ መንቀሳቀስ እንደማይችል መደንገጉን ከሽሬ የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

በውስጥ እና በውጭ ተወጥሮ ያለው የወያኔ ቡድን የራሴ ናቸው የሚላቸውን ካድሬዎቹን እንከዋን ባለማመኑ የተነሳ በየቦታው ግምገማ ላይ እንዲቀመጡ እያደረገ እርስ በርስ እያሻኮታቸው መሆኑን ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሰን ዘገባ ገለፀ::

ባለፈው ሳምንት ውስጥ የተጀመረው ይሄው ግምገማ በተለያዩ የጦር ካምፕ ውስጥ እየተደረገ ሲሆን በፍቼ የጦር ካምፕ፣ በጦላይ የጦር ካምፕ፣ በሁርሶ የጦር ካምፕ፣በናዝሬት ከተማ በአዲስ አበባ

ደምቦስኮ እና በሌሎች ማሰልጠኛ ጣቢያዎች ውስጥም ተመሳሳይ ግምገማ እየተደረገ መሆኑ ታውቆዋል::

በፍቼ የጦር ካምፕ ውስጥ የተጀመረው ለአንድ ወር ከ15 ቀናት የሚዘልቀው ይሄው የወያኔ ካድሬዎች ግምገማ እርስ በርስ እንዲወራረፉ ከማድረጉም በላይ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሲሰሩ የነበሩት እና በአሁን ሰዓት ስልጣን ላይ ያሉት ካድሬዎች መሆናቸውን ያስታወሰው የደረሰን ዘገባ በተለይ ከዚሁ ከሚደረገው ግምገማ በተጨማሪ መለስ ያዘጋጀው የፖለቲካ ትምህርት እንደሚሰጣቸውም ዘገባው አብራርቶዋል::

በዚሁ መለስ ያዘጋጀው የፖለቲካ ትምህርት እንደሚጠቅሰው ከሆነ ወያኔ በኢትዮጵያ ላይ ነግሶ ለመቀጠል እና ሌላ ጠንካራ ተቃዋሚ ቡድን እንዳይኖር ለማድረግ የሚያስችል ስልት እንዳለበት እና ስልጣኑም እዚያው ከወያኔ እጅ ሳይወጣ ለዘመናት እንደሚንከባለል የሚገልጽ መሆኑንም የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

በተመሳሳይ በጦላይ የጦር ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ የፌዴራል ፖሊስ አድማ በታኝ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊሶች፣ የኦሮሚያ ክልል ካድሬዎች በየተራ እየገቡ ግምገማ አድርገው የሚወጡበት ሲሆን ቀድመው የገቡት የኦሮሚያ ክልል ካድሬዎች ሲሆኑ በአሁኑ ሰዓት ግምገማው ተጠናቅቆ የተባረረው ተባርሮ ማስጠንቀቂያ የተሰጠውም ተሰጥቶት አርብ ግንቦት 7 ቀን 2001 ዓ.ም. የተሰናበቱ ሲሆን በምትካቸው አድማ በታኝ ፖሊሶች ትናንት ቅዳሜ ግንቦት 8 ቀን 2001 ዓ.ም. መግባታቸው ታውቆዋል::

በሌሎችም ማሰልጠኛዎች ውስጥ ያሉት የወያኔ ካድሬዎች ተመሳሳይ ግምገማ የሚያደርጉ ሲሆን በተለይ የአድማ በታኝ ፖሊሶች ላይ ግምገማው ጠንካራና ብዙ ፖሊሶች ሊሰናበቱበት ይችላሉ ተብሎ ስጋት ያሳደረ መሆኑን ዘገባው ገልጾዋል::

ይህ እየሆነ ባለበት በዚህ ወቅት በህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣናት መሀከል ከፍተኛ ሽኩቻ መፈጠሩን የውስጥ አዋቂ መንጮች ገለፁ:: እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ገለፃ ከሆነ በአድዋ ተወላጅ እና በተቀረው የትግራይ አውራጃ ተወላጆች መሀከል የተከሰተ የመንደር ፀብ መሆኑን ገልፀዋል::

ከታች እስከ ላይ ድረስ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት ዘረኛና፣ ሀገራዊ ራዕይ የሌላቸው ጭፍኖች መሆናቸው የታወቀ ሲሆን በተለይ በህወሀት መሀከል የተጀመረው የመንደርተኝነት ፀብ የቆየ ቢሆንም ሰሞኑን እንደ አዲስ መከሰቱን ምንጮቹ ገልፀዋል::

ከመለስ ዜናዊ ጀምሮ የአድዋ ተወላጆች ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን በመያዛቸው የተበሳጨት የተቀሩት የትግራይ ተወላጅ የወያኔ ባለስልጣናት በትግል ወቅትም ቢሆን እኩል መስዋዕትነት ከፍለን የመጣን

ሆኖ ሳለ በመንደር ተከፋፍሎ የአድዋ ልጆች የተለየ ጥቅም እንዲያገኙ እና ቁልፍ ቦታዎች እንዲሰጣቸው በመደረጉ ኩርፊያ እና ፀቡ እየተባባሰ እንደመጣ የምንጮቹ ጥቆማ አስረድቶዋል።

ከጠቅላይ ሚኒስትርነት እስከ ማዕከላዊ ምርመራ፣ የደህንነት ቁልፍ ቦታዎችና የፌዴራል ፖሊስ አድማ በታኝ አዛዦች ጭምር የአድዋ ተወላጆች መሆናቸውን ያስወሱት ምንጮቹ በዚህ አድልኦ የተነሳ የተቀሩት የትግራይ ተወላጅ ወያኔዎች በእነ መለስ ዜናዊ ላይ ቅሬታ ሲያቀርቡ የነበረ ሲሆን አሁን ግን ኩርፊያው ተባብሶ ወደ ፀብ ደረጃ መሸጋገሩን ገልፀዋል።

ከዚህም የተነሳ የተቀሩት የትግራይ ተወላጅ የወያኔ ባለስልጣናት የአንድ ሰው የስልጣን እድሜው ገደብ ሊበጅለት ግድ ይላል በሚል ንትርክ ውስጥ ውስጡን እያነሱ ሲሆን እነ መለስም ከውጭ ጠላቶቻችን ለይተን አናያችሁም እያሉ እያስፈራሩዋቸው እንደሚገኙም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል።